## 2. ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖዎች

ሙስና የወጣቶችን ሥራ አጥነት በማሳደግ፣ የትምህርትና የሥራ እድሎችን በመገደብ በወጣቶች ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚመደብ ሀብት ለተገቢዉ አገልግሎት እንዳይዉል በማድረግ መሰረተ ልማቶች እንዳይስፋፉ የሀገር ኢኮኖሚ ላይ ለዉጥ ማምጣት የሚችሉ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸዉ ጊዜ እንዳይጠናቀቅ ከማድረጉም በላይ ሀገርን ለጠጨማሪ ወጪ የሚዳርግ ነዉ፡፡

የዘመድ አዝማድ አሰራሮች እንዲኖሩ በማድረግ፤ ክህሎትና እዉቀትን መሰረት ያደረገ አሰራር እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ በተማሩ ወጣቶች ላይ ብስጭት እና መገለል ያስከትላል፡፡ ከዚህም በላይ ሙስና ሥራ ፈጠራን ያዳክማል፣ ይህም የኢኮኖሚ ዕድገትንና የወጣቶች ልማት ላይ የበለጠ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡

## 3.የፖለቲካ ተጽእኖዎች

ሙስና በወጣቶች የፖለቲካ ምህዳር ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል ከነዚህም ዉስጥ ወጣቶች በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚኖራቸዉን ተሳትፎን እንዲገደብ ከማድረጉም በላይ የፖለቲካ መገለልን ሊያስከትል ይችላል፡፡

ይህ ደግሞ ወጣቶች ያላቸዉን እምቅ እዉቀትና አዉጥተዉ በሀገራቸዉ ላይ በእኔነት ስሜት እንዳይሳተፉ ከማድረጉም በላይ አንዳንድ ጥናት ዉጤት እንደሚያሳዩት በፖለቲካዉ ተስፋ እንዲቆርጡ በማድረግ ወደ አሸባሪ ፣ ጠበኛ እና ፅንፈኛ ቡድኖች እንዲቀላቀሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ሙስናን በመከላከል ረገድ የወጣቶች ሚና

### የግንዛቤ ማሳደጊያ ስራዎች ላይ መሳተፍ

ወጣቶች ብዙን ጊዜ እንደ ጥበብ ያሉ የሚያስተምሩና የሚያዝናኑ ፈጠራ ስራዎችን በመጠቀም የአመለካከት ለዉጥ ማምጣት የሚያስችሉ ስራዎችን መስራት የሚችሉ በመሆኑ በግንዛቤ ማሳደጊያ ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ በትምህርት ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ ወጣት ማህበራት፣ የኪነ-ጥበብ ክበባት በመጠቀም የሙስና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሊሰሩ ይገባል፡፡

### የወጣቶች ትምህርት

ወጣቶችን ሙስና ስለሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽእኖዎች ማስተማር ሙስናን የመከላከያ ዘዴ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በናይጄሪያ እና በዩክሬን የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በውጤታማነት የተዘጋጀ ትምህርቶች በወጣቶች እና ተማሪዎች ላይ ብልሹ ባህሪን እንደሚቀንስ አረጋግጧል፡፡

### ፈጠራ

ወጣቶች አዲስ ነገር የመፍጠር እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የፀረ-ሙስና ትግል መፍጠርን፤ ወደፊት ማሰብ የሚፈልግ በመሆኑ ወጣቶች አዳዲስ ፈጠራዎችን ይዘዉ በመምጣት፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የራሳቸዉን አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡

### ክትትል እና ሪፖርት ማድረግ

ወጣቶች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ሙስና ሲፈፀም ወይም እንደሚፈፀም መረጃ ሲያገኙ ተከታትለዉ ለፀረ ሙስና ተቋም ጥቆማ በመስጠት የህዝብንና የመንግስትን ሀብት ከምዝበራ መታደግ ይችላሉ፡፡

### ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማድረግ

በፀረ ሙስና ትግሉ ወጣቶች በግንዛቤ ፈጠራዉም ሆነ በሙስና መከላከል ስራ ላይ በከፍተኛ ተነሳሽነት በመሳተፍ ትርጉም ያለዉ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን**

**21ኛው ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን በማስመልከት የተዘጋጀ**

# "ወጣቶችን ያማከለ የፀረ-ሙስና ትግል፤ የነገን ስብዕና ይገነባል"

**ህዳር 2017**

**አዲስ አበባ**

## ሙስና በወጣቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እና ሙስናን በመከላከል ረገድ ያላቸው ሚና

### መግቢያ

ሙስና በወጣቶች ሕይወት ውስጥ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ አሉታዊ ተፅእኖን የሚያስከትል አደገኛ በሽታ ነዉ። ወጣቶች የፀረ- ሙስና እንቅስቃሴዎችን ተረድተው ሙስና በሀገር ላይ ስለሚያስከትለዉ ዘርፈ ብዙ ተጽእኖዎች ግንዛቤ በመፍጠር በግል ተነሳሽነት እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለወጣቶች ተሳትፎ ትርጉም ያለው እድሎችን ሊሰጡ ይገባል።

### የሙስና ተጋላጭነት ደረጃ

በተለያዩ ሀገራት የወጣቶችን የሙስና ተጋላጭነት የሚያሳዩ ጥናቶች ተካሂደዋል። ጥናቶቹ እንደሚያሳዩት ወጣቶች ከሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች አንፃር ለሙስና የበለጠ ተጋላጭ እንደሆኑ ነው። ለምሳሌ፣ የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የ 2019 ግሎባል ሙስና የዳሰሳ ጥናት ውጤት እንዳረጋገጠው ከ18 እስከ 34 ዓመት የሆናቸው ምላሽ ሰጪዎች ጉቦ የመስጠትና እና የመቀበል እድላቸው 55 አመትና እና ከዚያ በላይ ከሆኑ ሰዎች በእጥፍ ይበልጣል (ዱሪ 2020)።

በተመሳሳይ፣ ከግሎባል ሙስና ባሮሜትር ኤዥያ 2020 የተገኙ ውጤቶች ከ18 እስከ 34 ዓመት የሆናቸው ወጣቶች ጉቦ የመክፈል ወይም ጥቅማጥቅሞችን ለመቀበል የሚያደርጉት ጥረት ከ 55 አመትና ከዚያ በላይ ከሆኑ ሰዎች የበለጠ እንደሆነ ያሳያል። (Transparency International 2021)። በተመሳሳይ በኬንያ እ.ኤ.አ በ2017 በሀገሪቱ ውስጥ ለወጣቶች በተደረገ ጥናት 46% ምላሽ ሰጪዎች ጉቦ እንደሚከፍሉ እና እንደሚቀበሉ ገልፀዋል።

በአጠቃላይ ከላይ የተመለከታቸዉ በተለያዩ አካላት የተሰሩ ጥናቶች የሚያሳዩት ወጣቶች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ሙስና ላይ የመጋለጥ እድላቸዉ ከሌሎቹ የእድሜ እርከኖች ከፍተኛ እንደሆነ ነዉ።

### ወጣቶች ለሙስና ያላቸው አመለካከት

ወጣቶች የሙስና ተጋላጭነት ደረጃን ከመለካት ባለፈ የወጣቶችን አጠቃላይ የሙስና አመለካከት የሚለኩ ጥናቶች ተሰርተዋል። የጥናቶቹ ዉጤቶች ጠቅለል ተደርገዉ ሲታዩ ወጣቶች በአብዛኛዉ ሙስና ተቀባይነት የሌለዉ ተግባር እንደሆነ እና አሉታዊ ተፅእኖዎች እንዳሉት እንደሚገነዘቡ ያሳያሉ። ይሁን እንጂ በአንዳንድ አገሮች የሚገኙ ጥቂት ወጣቶች ሙስና ተቀባይነት ያለው ተግባር እንደሆነ የሚያምኑ ወጣቶች እንዳሉ በጥናቶቹ ተመላክቷል።

ወጣቶች በአጠቃላይ ሙስናን መቃወማቸውን የሚገልፁ መረጃዎች የሚያሳዩ ቢሆንም አንዳንዶች እንደ መደበኛ ወይም የተለመደ ተግባር አድርገው እንደሚወስዱት ይጠቁማሉ። ይህ ማለት ወጣቶች ሙሉ ለሙሉ ሙስና በሀገርም ሆነ በህዝብ ላይ የሚያደርሰዉን ዉድመት ያለመገንዘብ አዝማሚያ የሚያሳይ በመሆኑ የወጣቶችን በሙስና ላይ ያላቸውን ግንዛቤ በአግባቡ ማስጨበጥ ከምንም በላይ ጊዜ የማይሰጠዉ ተግባር መሆኑን ያሳያል።

በስነ ምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን
ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

አድራሻ
በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና
ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ

ጥቆማ ለመስጠት
የነፃ ስልክ መስመር
8887
እንዲሁም በመስመር ስልክ
011 126 61 87
011 126 61 72

Addis Ababa Ethics and Anti-Corruption -ፀረ ሙስና
Addis Ababa Ethics Media
aanticoruption@gmail.co

## ሙስና በወጣቶች ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖዎች

### 1. ማህበራዊ ተጽእኖዎች

ሙስና ከፍተኛ ማህበራዊ ተጽእኖዎች አሉት፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

- ✦ የእምነት መሸርሸር፡ ወጣቶች በተቋማት፣ አስተዳደርና በሀገራቸው ላይ ያላቸው እምነት ይቀንሳል፣ የህብረተሰቡን በጋራ የመኖር እሴት እና የእርስ በእርስ መተማመን ስርዓትን ይሸረሽራል።
- ✦ ድህነትን ማባባስ፡ ሙስና በሁሉም የኢኮኖሚ ደረጃ ያሉ ወጣቶችን የሚጎዳ ሲሆን በተለይ ደግሞ ስራ አጥና ድህነት ላይ ያሉ ወጣቶች ላይ የሚኖረዉ ጫና ከፍተኛ ነዉ። ሙስና እንደ ጤና እና ትምህርት ያሉ አስፈላጊ አገልግሎቶችን በተገቢዉ ለወጣቶች እንዳይደርሱ በማድረግ ድህነት እንዲባባስ ያደርጋል።
- ✦ ማሕበራዊ አለመረጋጋት፡- ሙስና ፖለቲካዊ አለመረጋጋትን በመፍጠር፣ ወጣቶች በመሪዎቻቸው ላይ እምነት እንዳይኖራቸዉ በማድረግ፣ ተስፋ የቆረጠ ማህበረሰብ እንዲፈጠር ከማድረጉም በላይ ወደ ህዝባዊ አመፅ በመምራት ማህበረሰባዊ ቀዉስን ሊያስከትል ይችላል።
- ✦ የሞራል ዝቅጠት፡ ሙስና የህብረተሰቡን የሞራል እሴቶች ማሽቆልቆል፣ ኢ-ስነ ምግባር የጎደለው ባህሪን መደበኛ እንዲሆን እና ማህበራዊ ትስስርን በማባላሸት ኢሞራላዊ ትዉልድ እንዲፈጠር አስተዋፅዖ ያደርጋል።

**"Uniting with Youth Against Corruption:**
**Shaping Tomorrow's Integrity".**